## «እኔ እንደወደድኩዋችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህቺ ናት።»

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ያስተምር በነበረበት ወቅት ከሕግ አዋቂዎች (ፈሪሳ ወያንና ሰዱቃውያን) አንዱ ከሕግጋትህ ሁሉ ማንኛይቱ ትእዛዝ ትበልጣለች ብሎ ሲጠይቀው «እግዚአብ ሔር አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህ በፍጹም አሳብህ ውደደው። ሁለተኛይቱ ባልንጀራህን እ ንደነፍስህ፤ እንደራስህ፤ አድርገህ ውደድ የምትለዋ ናት።» በማለት መልሶለታል። (ማቴ. 22፣37-4) ይህንኑ ሕግ በበለጠ ወንጌላው ቅዱስ ዮሐንስ እንዲህ በማለት ያብራራዋል፤ «እግዚአብሔር ፍቅር ነው ፍቅር የ ሌለው እግዚአብሔርን አያውቅምና። እንዲሁም ማንም እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠ ላ፤ በተቸገረ ጊዜ ባይረዳው ቢያማው ሐሰተኛ ነው። የሚያየው ወንድሙን  የማይወድ ያላየውን እግዚአ ብሔርን እንዴት ሊወድ ይችላል? እግዚአብሔርን የሚወድ ወንድሙን ደግሞ እንዲወድ ይህቺ ትዕዛዝ ከ እርሱ አለች ይላል።» (1ኛ ዮሐ. ም 4 ፣ 8-1) ብርሃናተ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስም ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መጀመሪያ መልእክቱ (ምዕ. 13፣1-13) ላይ ፍቅር ከሌለን በመላእክት ልሣን እንኳዋን እስከመናገ ር ብንችል ከንቱ እንደሆንን ይናገራል።

በሰዎች መካከል ፍቅር እንዳይኖር አዳምን ያሳተ ዲያብሎስ ዛሬም ተንኮሉን አልተወውም። ከነዚህ አሳ ሳች መንገዶች ዋና ዋናዎቹ፤ በወንድማማች መካከል ሀሜት፣ አለመተማመንን፣ ተንኮል የመሳሰሉትን መ ፍጠር ነው። ሀሜት ትልቅ ኃጢአት ለመሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለያዩ ቦታወች ተገልጿል። ሀሜት ለፍቅር አለመኖር ዋና መንስኤ መሆኑ ጥርጥር የለውም። ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ በመልእክቱ ምዕ. 4፣11 «ወንድሞች ሆይ እርስ በእርሳችሁ አትተማሙ ይላል።»

መዋደዳችን ምን መምሰል እንዳለበት ለማስመልከት እግዚአብሔር አምላክ ዓለሙን ሁሉ ስለወደደ ዓለ ምን ለማዳን አንድያ ልጁን ወደ ዓለም ላከ። እርሱ ስለኛ ነፍሱን አሳልፎ በመስጠት ፍቅሩን አሳውቆናል ።1ኛ ዮሐ 3፣16 ታዲያ እኛም እንዲሁ ስለሌሎች ወንድሞቻችንን ፍቅር ጥቅም ስንል ሕይወታችንን እ ንኩዋን መሥዋዕት ማድረግ ይገባናል። የዘህ ሁሉ ማሰሪያውና መደምደሚያው እርስ በርሳችን መዋደድ መፋቀር ፣ አንዱ ስለአንዱ ይበልጥ ብሎ ማሰብ ነው። ለዘህም ነው ጌታ «እኔ እንደወደድኩዋችሁ እር ስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህቺ ናት።ዮሐ. 15፣12» ብሎ ያስተማረን።

ስለዚህ አምላካችንን በፍጹም ፍቅር በአንድ ላይ ሆነን በፍቅር እንድናመልክ፤ አካሄዳችንም እንደኛ አስ ተሳሰብ ወይንም ፈቃድ ሳይሆን እንደ አምላካችን ቃል መሆን ይኖርበታል። ቃሉን የምናደርግ እንጅ የ ምንሰማ ብቻ መሆን አይገባንም። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘጠና ዘጠኙን መላእክቱን ት ቶ የጠፋውን አዳምን ሊፈልግ እንደመጣ ሁሉ እኛም በተለያየ ምክንያት ከአፀደ ቤ/ክን ደጃፍ የቀሩትን ወገኖቻችንን የቀሩበትን ምክንያት በመጠየቅ፣በመመካከር፣ በመተራረም ማሰባሰብ እና ተመልሰው የሚመ ጡበትንመንገድ መፈለግ ይኖርብናል። ቤተ ክርስቲያን የቂምና የበቀል ቦታ ሳትሆን የተዋሕዶ አማኞች ኢትዮጵያውያን እና የክርስትናን እምነት በሚገባ ለተረዱ ሁሉ በፍቅር በአንድነት ሆነው በምሥጋና የሚ ኖሩባት ቤታቸው ነች።

ምናልባት በቤ/ክ አገልጋዮችና ተገልጋዮች መካከል አልፎ አልፎ በሚነሳው የሃሳብ ልዩነት ቅርየተሰኙ ወ ገኖች ቢኖሩ ከእነርሱ ጋር ያለንን አለመግባባት በረጋ መንፈስ በቅንነት በመነጋገር፣ በመወያየት አስወግደ ን በቀሪው ጊዜያችን ንስሐ ገብተን አንድ በመሆን ለመንፈሳዊ ሥራ መፋጠን ይኖርብናል። እንዲሁም የ በደለ እንኩዋን ቢኖር ይቅር መባባል እንደሚገባንም የአምላካችን ቃል ግልጽ አድርጎ ያስረዳናል። ለእም ነታችንና ለአንድነታችን ዋና መሠረቱ ፍቅር በመሆኑ እርስ በርሳችን በመዋደድ መጠናከር እንጂ ለጥልና ጭቅጭቅ ቦታ ሊኖረው አይገባም። የአምላካችን ቃልማ ባልጀራችንን ብቻ ሳይሆን ጠላቶቻችንም ጭም ር መውድድ እንዳለብን ይነግረናል።

ነገር ግን ፍቅር በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ እንዳይሰፍን ሆን ብሎ እንቅፋት ለሚሆኑ (ለሆኑ) ካህናትም ሆነ ምእመናን በንስሐ እስካልተመለሱ ድረስ አምላካችን ለቤቱ ቀናተኛ ነውና ፍርዱ የማይቀር ነው። እ ግዚአብሔር አምላክ እንደ እኛ ለበቀል የፈጠነ አይደለም፤ ይታገሳል፣ ለንስሐ ጊዜ ይሰጣል። በኦሪቱ ዘ መን ሰዎች ከእግዚአብሔር ሕግ ሲወጡ ወዲያው ይቀሰፉ እንደነበር በብሉይ ኪዳን ብዙ ቦታ ላይ ተጽ ፎ እናገኛለን። በአሁኑ ዘመን ያን የመሰለ መቅሰፍት የለም እያሉ አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔርን በመዳ ፈር ብዙ በደል ሲፈጽሙ ፣ ቤተ ክርስቲያን ሲበድሉ፣ የክርስቶስ ወገኖችን ሲያስቀይሙ፣ በአፀደ ቤተ ክርስቲያን ፍቅር እንዳይኖር ሲተጉ ይታያሉ። የአሁኑ ዘመን የመቅሰፍት መጀመሪያው ስሜት ቀበዘባዛ መሆን፣ ደስተኛ አለመሆን፣ እንቅልፍ ማጣት፣ በኑሮ አለመደሰት የመሳሰሉት ናቸው። ከዚህ መቅሰፍት ለመዳን፣ ከአምላካችንበረከትን ለማግኘት በፍጹም ሕጉን ልንጠብቅ፣ እርስ በርሳችን ልንዋደድ፣ ፍቅር በ

እኛ መሃከል እንዲጸና ልንጸልይ ፣ ልንጥር ፣ የሰዎችን በደል ላናስብ ይገባል። ሰዎች እንኳን ቢበድሉን ይቅር ማለትን መልመድ አለብን። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ሲያስተምር ከሐዋርያቱ አንዱ የሆነው ቅዱስ ጴጥሮስ ወደ ጌታ ቀርቦ «ጌታ ሆይ ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ልተውለት? እስከ ሰባት ጊዜን? አለው። ኢየሱስ እንዲህ አለው- እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ እስከ ሰባት ጊዜ አልልህም። ማቴ.18 ፣21» እንዲሁም በዚሁ ወንጌል ምዕራፍ 5 ቁጥር 22 ላይ «እኔ ግን እላችኋለሁ፤ በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል ፤ ወንድሙንም ጨርቃም የሚለው ሁሉ የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል። እንግዲህ መባህን በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ በዚያም ወንድምህአንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ፤ በዚያ በመሠዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ በኋላም መጥተህ መባህን አቅርብ ።» ስለዚህ እርስ በርሳችን እየተዋደድን፣ በመከባበር፣ አንዱ የአንዱን ነውር ኃጢአት ለመግለጽ ሳንሸቀዳደም ነገር ግን በክርስቶስ ፍቅር እየተወቃቀስን፣ እየተራረምን፣ ይቅር እየተባባልን በፍቅር ልንኖርና ቤተ ክርስቲያናችን ልናገለግል ይገባል።

በፍጹም ሰውነታችን እግዚአብሔርን ልንፈራው ፣አገልጋዮቹን ካህናትንም እንድናከብራቸው ተጽፎአል። (መጽ. ሲራክ 7፣29) ይሁን እንጅ ካህን በመሆን ብቻ ንጽህና ቅድስና ይገኛል ማለት አይደለም። ለዚህም የእግዚአብሔር ነቢይ የሆነው ኤርምያስ ። «የማሰማሪያዬን በጎች ለሚያጠፉና ለሚበትኑ ወዮላቸው! ይላል እግዚአብሔር፤ ...... በጎቼን በትናችኋል ፣ አባራችዋቸውማል አልጎበኛችኋቸውም እነሆ የሥራችሁን ክፋት እጎበኝባችኋለሁ ይላል እግዚአብሔር።» ትን. ኤር ም 23፣1-3 ይህ ማለት ደግሞ ከቤተ ክርስቲያን ተሰናክለው ለሚቀሩ ተጠያቂዎች ካህናት ብቻናቸው ማለት አይደለም፤ እያንዳንዱም ምእመን ጭምር እንጅ። ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ሲያስተምር ።በእኔ ከሚያምኑ ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን ያሰናከለ የወፍጮ ድንጋይበአንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቅ ባሕር መስጠም ይሻለው ነበር።ማቴ 18፤5» ያለውን ማስታወስ ይኖርብናል።

ስለዚህ እያንዳዳችን እንደ ሕጉ ልንኖርና ስለሌሎች ወንድሞቻችን መንፈሳዊም ሆነ ሥጋዊ ሕይወት ልናስብ ፤ በእኛ የተሳሳተ አካሄድ እንዳይሰናከሉ ልንጠነቀቅ ይገባል። በተለይ ይህ የጾም ወቅት ስለሠራነው በደል፣ ስላስቀየምናቸው ሰዎች የምንፀፀትበት፣ ኃጢአታችን እንዲሠረይልን፣ ምሕረትን የምንጠይቅበት ወቅት ነው። ስንጸልይም ስለ እኛ ብቻ ሳይሆን ስለ ሌሎች ወገኖቻችን፣ ስለ ሀገራችን፣ ስለ ዓለሙ ጭምር መሆን አለበት። ልመናችን፣ ጥያቄያችን አግባብ ያለው እስከሆነ ድረስ በፍጹም የሚደረግልን መሆኑንም ማመን አለብን። በመጽሐፈ ሲራክ ምዕራፍ 2፤10 ላይ እንዲህ ይላል «በዘመን የቀደሙ ሰዎችን አስተውሉ በእግዚአብሔር  አምኖ ያፈረ ማነው? እወቁ እሱን በመፍራት መከራውንም የታገሠ በመከራ እንደጣለው የቀረ ማነው። ለምኖትስ ቸል ያለው ማነው። እግዚአብሔር ይቅር ባይ ነውና ርኅሩኅ ነውና ኃጢአትን ይቅር ይላል ከመከራም ቀን ያድናል።» ስለዚህ ፍጹም ጠንካራ እምነት ሊኖረን ይገባል። ቅዱስ ዳዊትበመዝሙሩ «አቤቱ ንጹህ ልብን ፍጠርልኝ፣ የቀናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ» እንዳለው እኛም አምላካችን ይህን እንዲያደርገልን በጸሎት ልንጠይቀው ይገባል።

መልካም የጾም ሳምንታት!

በእደ ማርያም እጅጉ ረታ

የካቲት 1997